ሠ. 1. የአዳምና የሔዋን ክፋት የእግዚአብሔርን መልካም ሥራዎች በዛሬው ዓለማችን ውስጥ ጭምር አበላሽቷል ለማለት የምንችለው በምን መንገድ ነው?

2) ይህስ አብያተ ክርስቲያናታችንን እንዴት ይጎዳል?

3) ሕይወታችንንስ?

ረ. 1) እያንዳንዱ ተማሪ ከዚህ ቀደም የዘፍጥረት መጽሐፍ ለመንፈሳዊ እድገቱ እንዴት እንደረዳው ለቡድኑ አባላት ያካፍል።

2) እያንዳንዱ ተማሪ ከዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ለመማር ስለሚፈልጋቸው ነገሮች ለሌሎች ያካፍል።

5. ጸሎት - እግዚአብሔር የተማራችሁትን በተግባር እንድትፈጽሙ እንዲረዳችሁ በመጠየቅ ስብሰባውን በጸሎት ፈጽሙ።

ትምህርት ሁለት

ዘፍጥረት 1-2፡3

መጀመሪያ ቀን ዘፍጥረት 1፡1-2

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ. የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ጽንሰ-አሳብ የዓለምን አጀማመርና ስለ ሁሉም ነገሮች፥ በተለይም ስለ ሰው አመጣጥ የሚያስተምረውን አጠር ባለ ጽሑፍ አቅርብ።

ለ. ክርስቲያኖች በትምህርት ቤት፥ እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ ያላቸውን እምነት ለመከላከል ያስቸግራቸዋልን? ስለ አዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ- አሳብስ የሚሰጡት ምላሽ እንዴት ነው?

ሁላችንም ስለ አዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ-አሳብ በትምህርት ቤታችን ተምረናል። ይህም የሆነበት ምክንያት ዛሬ ሳይንስ የሚያተኩርበት ዋና ጽንሰ-አሳብ በመሆኑ ነው። የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ-አሳብ ብዙ አመለካከቶች ቢኖሩትም፥ አንድ የወል የሆነ ትምህርት ግን አለው። ዛሬ የምናያቸው ሕይወቶች ሁሉ፥ ነገሮች ወደ በለጠና ከፍ ወዳለ

ሕይወት በማደጋቸው፥ በተፈጥሮ የተገኙ ናቸው ይላል። ከምንም ተነሥቶ ነገሮችን የፈጠረ ፈጣሪ አልነበረም። እነርሱ የሚያምኑት በብሊዮን ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት፥ ምናልባትም በፕላኔቶች ግጭት ሳቢያ፥ በሕዋ ውስጥ በተከሰተው ፍንዳታ ፀሐይ እና ጭፍሮችዋ (ሶላር ሲስተም) እንደተገኙ ነው። ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ እንደ አሜባ ካለው ከአንድ ሕዋስ (ሴል) ፍጥረታት ተነሥቶ በቢሊዮን በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ አጥቢዎችን ወደሚያህል ውስብስብ የሕይወት ደረጃ እንዳደገ ያስተምራሉ። ሰውም ከአንዱ የአጥቢያዎች ዝርያ አዝጋሚ በሆነ የለውጥ ሂደት ተሻሽሎ፥ ዛሬ እንደምንመለከተው የዓለም ጌታ ሊሆን በቃ። ስለዚህ በዚህ የአዝጋሚ ለውጥ ዕድገት ውስጥ፥ ሂደቱ ሁሉ ተፈጥሮአዊ ስለሆነ፥ ዓለምን ፈጠረ ለሚባለው እግዚአብሔር ሥፍራ የለውም በማለት ይደመድማሉ።

ክርስቲያን ሳይንቲስቶች ኢ-አማንያን ሳይንቲስቶች ለሚያቀርብዋቸው አመለካከቶች ብዙ መልሶች አሉዋቸው። እኛ ክርስቲያኖች ሁሉን ነገር በፈጠረ አምላክ በማመናችን መፍራት የለብንም። ሰው ሳይሠራው አንድ ነገር በምድር ላይ እንዲሁ ሊሆን እንደማይችል ሁሉ፥ እግዚአብሔር እስከሌለ ድረስ ዓለምም ልትኖር እንደማትችል ሥነ-አመክንዮ(ሎጂክ) አስረግጠ ይነግረናል።

እንደዚሁም ዓለምንና የሰው ዘርን የእግዚአብሔር አካላት እንደሆኑ አድርገው የሚያስቡ ሌሎች ወገኖችም አልታጡም። ይህም ሂንዱይዝምና ቡድሂዝምን የመሳሰሉ የበርካታ ምሥራቃውያን ሃይማኖቶች አመለካከት ነው። ሰው፥ ዛፎችና ሌሎችም ነገሮች ሁሉ የአምላክ ክፍሎች ናቸው ይላሉ። በተጨማሪም ብዙ አማልክት እንዳሉ ያስተምራሉ። ይህ ትላልቅ ዛፎችን፥ ትላልቅ ወንዞችን፥ ወይም ሌሎች ያልተለመዱ ነገሮችን፥ አማልክት አድርገው ይቆጥሩ ከነበሩት ከጥንት ሰዎች ጥንታዊ ሃይማኖት ጋር ይመሳሰላል። እነዚህን እምነቶች የሚያራምዱ ሰዎች በእግዚአብሔርና በፍጥረታት መካከል ብዙም ልዩነት አያደርጉም።

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ. በኢትዮጵያ የተለያዩ ሰዎች ከእነዚህ ከሁለቱ አመለካከቶች በአንዱ የሚያምኑት እንዴት ነው?

ለ. የአንተስ አመለካከት ምንድነው? ለምን?

እነዚህ ሁለቱም አመለካከቶች ስሕተቶች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው፥ እኛ የእራሱ ባሕርይ ባለው በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ተፈጥረናል። የገዛ ባሕሪይ ያለው እግዚአብሔር ስንል፥ ኃይል ብቻ ሳይሆን፥ የሚያስብ፥ የሚሰማና የሚያቅድ፥ ወዘተ. ማለታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር በስተቀር፥ ሁሉም ነገር እንደተፈጠረ ያስተምራል። እዚአብሔር ብቻ አልተፈጠረም። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ባለው ዓለም ውስጥ እንደምንኖር ያስተምራል። እግዚአብሔር ዓለምን ለአንድ ምክንያት መፍጠር ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን የዓለምን ክስተቶች ወደ አንድ ፍጻሜ እየመራ ነው። እነዚህን ሁለት ዋና ዋና ትምህርቶች በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እናገኛለን። የክርስትናን ተከታዮች በአዝጋሚ ለውጥ፥ ከሚያምኑት ወይም ራሳቸውን የአምላክ አካላት አድርገው ከሚቆጥሩት የሚለዩዋቸው እነዚህ ሁለት ትምህርቶች ናቸው።

3ኛ ጥያቄ፡ - እነዚህ ሁለት እውነቶች ለክርስቲያኖች አጽናኝ የሚሆኑት እንዴት ነው?

በዚህ ሳምንት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት የሚያስተምረውን እናጠናለን። እግዚአብሔር እንዴት እንደፈጠረ ከሚተርከው የዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ ብዙ ጥያቄዎች ሊኖሩን ይችላሉ። አንዳንድ ልናውቃቸው የምንፈልጋቸው ነገሮች የተደበቁ ናቸው። ለምሳሌ እግዚአብሔር መላእክትን መቼ እንደፈጠረ፥ ወይም ሰይጣን ከየት እንደመጣ አናውቅም። ነገር ግን የዘፍጥረት ጸሐፊ ለእነዚህ ጥያቄዎች ትኩረት አልሰጠም። የእርሱ ዓላማ የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ የሆነውን የእግዚአብሔርን ችሎታና ኃይል ማሳየት ነበር። በተለይም እግዚአብሔር ዓለምንና በዓለም ውስጥ እንዲኖር ሰውን እንዴት እንደፈጠረ ለማሳየት ፈልጓል። በዕብ. 11፡3፥ እንደሚለው «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል አንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን»። የዓለምን ጅማሬ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄያችንን ሁሉ ባይመልስም፥ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ሐቅ አድርጎ በማቅረብ፥ በእምነት እንድንቀበለው ይጠይቃል። የአፈጣጠሩም ሁኔታ፥ የማወቅ

ጉጉታችንን በመቀስቀስ እግዚአብሔርን እንድንጠራጠር ሳይሆን፥ ይልቁንም እንድናመሰግነው ሊገፋፋን ይገባል።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ወደ ዘፍጥረት 1-2 ጥናታችን ከመሄዳችን በፊት፥ መዝሙር (19)፡ 1-4 አንብብ። መዝሙረኛው ፍጥረት ሁሉ ምን ያደርጋል ይላል?

ለ) እግዚአብሔርን ለእኛ ስላበጀው አስደናቂ ፍጥረቱ ለማመስገን የተወሰነ ጊዜ ውሰድ።

5ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 1-2፡3 አንብብ። በየዕለቱ የተፈጠሩትን ልዩ ልዩ ፍጥረታት ዘርዝር።

6ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 1፡ 1-2 እንደገና አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ፡- ሀ) በመጀመሪያም ሲባል የተጠቀሰው የትኛው መጀመሪያ ነው?

ለ) በቁጥር አንድ እግዚአብሔር እንደፈጠራቸው የተገለጹት ሁለት ዓበይት ነገሮች ምንድናቸው?

ሐ) በእነዚህ ሁለት ነገሮች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ነገሮች ምንድናቸው?

መ) በቁጥር 2 ላይ ምድር በምን በምን መንገዶች ነው የተገለጸችው?

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ፥ የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሐፊ ዋና ዓላማ፥ በኋላ የአብርሃምና የአይሁዶች አምላክ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ማሳየት ነው።

ጸሐፊው ዓለም እንዴት እንደተጀመረ ለማሳየት ቢፈልግም እንኳ፥ ያተኮረው በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ላይ አይደለም።

7ኛ ጥያቄ፡- ዓለም እንዴት እንደተፈጠረ በባሕልህ የሚነገር አንድ ተረት ጻፍ።

የሁሉም ዓለም ባሕሎች ዓለምና ሰው እንዴት እንደተፈጠሩ የሚናገር ታሪክ አላቸው ለማለት ይቻላል። በአንዳንዶች ዘንድ የእግዚአብሔር ሚስት የሸክላ ቅርጻ ቅርጾች አበጅታ በእሳት

ስትጠብሳቸው ወደ ተለያዩ ሰዎች ተለወጡ የሚል ታሪክ አለ። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ስሕተቶች ናቸው። በመጀመሪያ የሆነውን ነገር ለመረዳት፥ በመጀመሪያ ወደነበረው ወደ እግዚአብሔር መሄድ ያስፈልገናል። ሁሉም ነገር እንዴት እንደተጀመረ የመናገር ብቃት ያለው እርሱ ብቻ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስን የፍጥረት ታሪክ ልዩ መሆን ለመረዳት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለተጻፈበት ዘመን ትንሽ ማወቅ ያስፈልገናል። በሙሴና በእስራኤል ሕዝብ ዘመን፥ ከእስራኤል በስተቀር፥ ሌሎች ሕዝቦች በብዙ አማልክት ያምኑ ነበር። ከዋክብቶችን፥ ፀሐይን፥ ጨረቃን፥ ወንዞችንና ሌሎች በርካታ ነገሮችን አማልክት አድርገው ያመልኩባቸው ነበር። አማልክትን ከሰብዓዊ ፍጡራን ትንሽ የሚበልጡ ነገር ግን እንደ ሰዎች ዓይነት ባሕሪይ የተላበሱ አድርገው ይመለከቷቸው ነበር። አማልክቱ እንደሚጋቡ፥ እንደሚወልዱ፥ እንደሚገዳደሉ፥ ወዘተ. አድርገው ያስቡ ነበር።

ለምሳሌ ፍጥረተ-ዓለምን በተመለከተ እጅግ ታዋቂ የሆነውና አብርሃም ከመጣበት አገር የሚነገረው ታሪክ እንዲህ ይል ነበር። ባቢሎናውያን ‹ቲያማት› የምትባል ክፉ እንስት የውቂያኖስ አምላክ ያመልኩ ነበር። ይህች አምላክ ‹አኑ› ከሚባለው ከትልቁ አምላክ ጋር ጦርነት ገጠመች። ዳሩ ግን ‹ቲያማት› ‹አኑ›ን ከማሸነፍዋ በፊት ‹ማርዱክ› የሚባል ሌላ አምላክ ተነስቶ ‹ቲያማት›ን ገደላት። እርሱም የቲያማትን አካል ወስዶ ለሁለት ከፈለው። እነዚህም ለሁለት የተከፈሉት ሰማይና ምድር ሆኑ። ከዚያም ሌሎቹ የተለያዩ ተባዕታይና አንስታይ አማልክት ሰውን ፈቃዳቸውን እንዲፈጽም ባሪያቸው አድርገው ሠሩት። ሰው ምንም ክብር አልነበረውም፤ ሰዎች የአማልክት አሽከሮች፥ ባሪያዎች ነበሩ።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት ከዘገበው በምን ይለያል?

ለ) እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ባለው መረዳትና ከሌላው ሰው ጋር ባለው ግንኙነት ላይ አደገኛ የሚሆነው እንዴት ነው?

ጸሐፊው የፍጥረትን ታሪክ የጻፈው፥ በእግዚአብሔርና በፍጥረት ሥራ ላይ የሚሰነዘሩትን እንዲህ ዓይነቶቹን የተሳሳቱ አሳቦች ለመዋጋት ነበር። የአብርሃም አምላክ የሆነው አንድ አምላክ ብቻ አለ። ለዚህ ነው የዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያ ቁጥር፥ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ብሎ የሚጀምረው።

ዘፍጥረት 1፡1 ከምዕራፍ 1-2 ላሉት ሌሎች ክፍሎች የማጠቃለያ ዓረፍተ ነገር ነው። በቀላል ዓረፍተ ነገር፥ መጽሐፍ ቅዱስ የፍጥረት ምንጭ ወደሆነው ወደ እዚአብሔር ያመለክታል። ‹ሰማይና ምድር› በግለት ጸሐፊው እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ በግልጽ ያመለክታል። ይህ ጥቅስ ብቻውን እውነተኛ ስለሆነው አምላክ ታላቅነት፥ ችሎታና ኃይል ይገልጻል።

በዚህ ጥቅስ ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ገለጻ አናገኝም። የተለያዩ ነገሮችን ከሚመስሉ ሌሎች የአሕዛብ አማልክት በተቃራኒ፥ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል፥ ወይም ባሕርያቱ ምን እንደሆኑ አልተነገረንም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚመስል ምንም ነገር ስለሌለ ነው። እግዚአብሔር ሥጋዊ አካል ወይም ቅርጽ የሌለው መንፈስ ነው።

አይሁዶች እግዚአብሔርን ለማመልከት ብዙ የተለያዩ ስሞች ተጠቅመዋል። እነዚህ ስሞች እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያሳዩ የተለያዩ ትርጉሞች ነበሩዋቸው። በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ የዕብራይስጡ የእግዚአብሔር ስም ‹ኤሎሂም› ነው። ሁሉ በሁሉ የሆነውን አምላክ ኃይልና ግርማ የሚያሳየው ይህ ስም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተለመደ ነበር። ጸሐፊው አንድ ፈጣሪ አምላክ ስለመኖሩ ግሳመኛ ነጥቦች ለማቅረብ አልሞከረም። ይልቁንም ጸሐፊው የፈጣሪ አምላክን ሥራ በመናገር ይጀምራል። ይሁን እንጂ በፍጥረት ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን ማንነትና ምንነት ማየት እንጀምራለን። እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል።

‹በመጀመሪያ› የሚለው ቃል ወደ ምንድነው የሚያመለክተው? ወደ እግዚአብሔር መጀመሪያ ነው፥ ወይስ ወደ ቁስ አካላዊ ፍጥረታት መጀመሪያ? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መጀመሪያ እንደሌለው

ያስተምረናል [መዝ.(90)፡2]። እርሱ ሁል ጊዜ፥ ከዘለዓለም በፊትም ኖሮአል - ይኖራልም። ዓለም ከመፈጠርዋ ከብዙ ዘመናት በፊት፥ ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው አስቀድሞ፥ ወይም ከፍጥረት ሁሉ በፊት እግዚአብሔር ነበር። ሰው እንደ መሆናችን፥ ግንዛቤአችን ውስን ነውና፥ ይህ ለመረዳቱ የሚያዳግት አሳብ ይሆንብናል።

«በመጀመሪያ» የሚለው ቃል የሚናገረው ስለ ፍጥረት መጀመሪያ ነው። የጊዜ፥ የቀናት፥ የወራትና የዓመታት መጀመሪያ ነው። እንዲሁም የሰው ዘር ታሪክ መጀመሪያ ነው። ሰው በምናቡ ኃይል ወደ ኋላው ተመልሶ ማሰብ እስከሚችልበት ጊዜ ድረስ ይርቃል። ያ ጊዜ በተለይም የእግዚአብሔርና የሰው ግንኙነት ታሪክ የተጀመረበት ወቅት ነው።

ዘፍጥረት 1፡1 እግዚአብሔር ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን እንደፈጠረ ይናገራል። አንደኛ፥ እግዚአብሔር ‹ሰማያት›ን ፈጥሯል። ሰማያት የሚለው ቃል በምድር ላይ የሌሉትን ነገሮች ሁሉ ያመለክታል። ሰማይ፥ ሕዋውና በውስጡ ያሉትን ሁሉ ማለት ነው።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ምድርን ፈጥሯል። ይህ በምንኖርባት ዓለም ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል። ሰማያት እንዴት እንደተፈጠሩ ጸሐፊው በጥቂቱ ብቻ ይናገራል። እርሱ ያተኮረው ሰው በሚኖርባት ምድር ላይ ነው። የእግዚአብሔር ፍጥረታት ቁንጮ የሆነው ሰው የሚገኘው በምድር ላይ ነው። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ሊያደርግ በታሪክ የታየው በምድር ላይ ነው። በእግዚአብሔርና በሰው ዘር፥ እንዲሁም በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የተደረገው ግንኙነት ታሪክ የታየው በምድር ላይ ስለሆነ፥ ምድር ለጸሐፊው በጣም አስፈላጊ ነች። ስለዚህ እነዚህ ሁለት ነገሮች (ሰማያትና ምድር) በአንድነት የተፈጠረውን ነገር ሁሉ የሚያመለክቱ ናቸው። እግዚአብሔር በነገሮች ላይ ገዥ ስለሆነ፥ ሁሉም ሊታዘዙት እንደሚገባ ያሳዩናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ‹ፈጠረ› የሚለው ቃል፥ ሁል ጊዜም እግዚአብሔር ከምንም ነገር አንድ ነገር ማስገኘቱን ወይም አንድን ነገር አዲስ ነገር አድርጎ የመሥራቱን ሁኔታ ያመለክታል። ከምንም ተነሥቶ አንድን ነገር ለመሥራት የሚችል ኃይል ያለው እዚአብሔር ብቻ ነው።

ፈጣሪ እርሱ ብቻ ነው። ሌላው ሁሉ ፍጥረት ነው። ሁሉን በፈጠረው፥ ሁሉን ቻይ በሆነው እግዚአብሔርና ለሀልውናቸው የእርሱን ጥገኝነት በሚሹት ፍጥረታት መካከል ታላቅ ልዩነት አለ።

9ኛ ጥያቄ፡- ኢሳ. 65፡17 እና ራእይ 21፡1 ተመልከት። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተተነበየው ምንድነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ትምህርትም እንደመጀመሪያው ሁሉ እግዚአብሔር እንደገና ሲፈጥር ያሳየናል። መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻ ዘመን እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚፈጥር ያስተምረናል። በዚህ ምድር ላይ ኃጢአት ያበላሸው ነገር ሁሉ አንድ ቀን ያልፍና በኃጢአት ከመበረዟ በፊት አዳምና ሔዋን ይኖሩባት የነበረችውን የመጀመሪያዪቱን ምድር በመሰለች ሥፍራ እንኖራለን።

ዘፍጥረት. 1፡2፥ በክርስቲያን ሊቃውንት መካከል ብዙ ግጭቶችን ያስከተለ ጥቅስ ነው። ዋናው ጥያቄ ‹ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ዓለምን እንደገና መፍጠር ከመጀመሩ በፊት የነበረውን የዓለም ሁኔታ የሚገልጽ ነው? ወይስ የቀሩት የምዕራፍ አንድ ክፍሎች ሁሉ የተመሠረቱበትን የመጀመሪያ የፍጥረት ደረጃዎችን የሚያመለክት?› የሚል ነው።

በቁጥር 2 ዓለም በአራት መንገዶች ተገልጻለች፡-

1. ዓለም ቅርጽ አልነበራትም። ሰዎችና እንስሳት እንዲኖሩባት በብቃት አልተዘጋጀችም ነበር። ዛሬ ተውባ እንደምናያት አልነበረችም። ስለሆነም ከጥቅም ላይ እንድትውል እንደገና መሠራት ነበረባት።

2. ዓለም ባዶ ነበረች። ዕፅዋት፥ አዝርዕት፥ ዛፎች፥ ወይም እንስሳትና ሰው አልነበረባትም። ለመሞላት እንደሚጠባበቅ ባዶ ምድረ በዳ ነበረች።

3. ዓለም ጨለማ ነበረች። የሚበራ ብርሃን አልነበረም። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የምድር ገለጻዎች አሉታዊ ባሕርይ ነበራቸው። መልካም ያልሆኑና መለወጥ የሚገባቸው ጠባያት ነበሩ። ቀሪው የፍጥረት ታሪክ የሚገልጸው እነዚህ ሦስት ነገሮች እንዴት ወደ አንድ ጥሩ ነገር፥ ማለትም ውብና ለሰው መኖሪያነት

ወደሚያመች ሁኔታ እንደተለወጡ ነው። አንዳንድ ሊቃውንት እነዚህን ሦስት ነገሮች የክፋት ምልክቶች አድርገው ይመለከቷቸዋል። በብሉይ ኪዳን፥ በምድር ላይ የኃጢአት ጥፋት ምድረ በዳ እንደሚፈጠር ሆኖ ታይቷል (ኤር. 4፡23፤ ኢሳ. 34፡11)። ጨለማም ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ሊያሸንፈው የሚገባ የክፉ ምሳሌ ሆኖ ነው የሚታየው (ለምሳሌ፥ ዮሐ. 1፡4-5፤ 12፡35-36 ተመልከት)።

4. የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር። እግዚአብሔር በመንፈሱ በምድር ላይ ስለነበረና በተስፋ-ቢስ ሁኔታ ውስጥ ያለች የምትመስለውን ምድር ይቆጣጠር ስለነበር፥ ይህ የመጨረሻው የምድር ገለጻ አዎንታዊ ባሕርይ ያለው ነው። ‹መንፈስ› የሚለው ቃል ‹እስትንፋስ› ተብሎ ሊተረጎም ቢችልም፥ ከተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት እንደምንረዳው፥ በዚህ ሥፍራ የተመለከተው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለ ዓለም ከተደረገው ገለጻ እንደምንመለከተው ምድር ባመዛኙ በውኃ የተሞላች ይመስላል። የፍጥረት ሥራ ወኪል የሆነው መንፈስ ቅዱስ፥ ከጎጆው ከፍ ብሎ ከሚያንዣብብ ንስር ጋር ተነጻጽሯል። ይንሳፈፍ የነበረው ዓለምን ለመጠበቅ ነበር። በተጨማሪም የፍጥረት ሥራውን ለመጀመርና ምድርን ገንብቶ ጠቃሚ መኖሪያ ለማድረግ ከመጓጓቱ የተነሣ ነበር።

ምንም እንኳ አንዳንዶች ቁጥር ሁለትን ስለ አዝጋሚው ለውጥ የመጀመሪያ ደረጃዎች የተሰጠ መግለጫ አድርገው ለመውሰድ ቢፈልጉና የመጀመሪያዋ ምድር በቢሊዮን በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ ብመለዋወጥ እኛ የምናውቃት ምድር ለመሆን በቅታለች ቢሉም፥ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገረው ጋር አይስማማም። እዚህ ላይ ዕብራውያን 11፡3፥ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደሆነ እንጂ ከነበረው በለውጥ ሂደት አደገ እንደማይል ልብ በል። ነገሮች ካለመኖር ወደ መኖር የመጡት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንጂ በአዝጋሚ ለውጥ ሂደት አይደለም።

እነዚህን ጥቅሶች በተመለከተ ሁለት ዋና ዋና ወግ አጥባቂ(ኮንሰርቫቲቭ) አመለካከቶች አሉ። አንደኛ፡- አንዳንድ

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በእርግጥ ሁለት ዓለማትን ፈጥሯል ብለው ያምናሉ። በእነርሱ እምነት ዘፍጥረት 1፡1 ስለ መጀመሪያው ዓለም መፈጠር ሲናገር፥ ዘፍጥረት 1፡2 ደግሞ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ፍጥረት እንዴት እንደጠፋ የሚያሳይ መግለጫ ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ ብለው ያምናሉ። ነገር ግን ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ጊዜ፥ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መሀከል የተካሔደው ጦርነት በመጀመሪያ የተፈጠረውን ዓለም አወደመው። ከብዙ ዓመታት ምናልባትም ምዕተ-ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር አሁን ያለውን ዓለም እንደገና ፈጠረ ወይም አደሰው። ይህ ነው በዘፍጥረት 1፡3-31 የሚታየው ታሪክ። ዛሬም እኛ የምንኖረው በዚህ እንደገና በተፈጠረ ዓለም ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠሩን በማስመልከት የሚነሳውን በርካታ የሳይንስ ተቃውሞ ለመከልከል ይህን አመለካከት በማብራሪያነት ይጠቀሙበታል። በመጀመሪያዋና በሁለተኛዋ ዓለም መካከል ረዥም የጊዜ ገደብ ከኖረ፥ አልማዞችን፥ የድንጋይ ከሰልና የነዳጅ ዘይት ለማስገኘት የሚያስፈልጉት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት አልፈዋል ማለት ነው።

10ኛ ጥያቄ፡- ኤርምያስ 4፡23-28፤ ኢሳይያስ 24፡1-3፤ ሕዝቅኤል 28፡12-19 ተመልከት።

ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ስለ ዓለም ሁኔታ የሚያስተምሩት ምን ይመስላል?

ለ) እነዚህ ጥቅሶች የተቀባ ኪሩብ ስለሚባለው ሰው ምን ያስተምራሉ?

ምንም እንኳ አንዳንድ ሊቃውንት ከእዚህ በፊት ስለ ጠፋችው ምድር ጠቋሚ ፍንጮች ቢያገኙም፥ እነዚህ ጥቅሶች ውድመቱ ስለ መጀመሪያዪቱ ምድር ይሁን ወይንም ስለ ሰይጣን ውድቀት በግልፅ አይናገሩም። የመጀመሪያው አቋም በዘፍጥረት 1፡2 ላይ ባለችው መረዳት ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው።

ሁለተኛው አመለካከት እግዚአብሔር አሁን የምንኖርባትን አንድ ዓለም ብቻ እንደፈጠረ የሚናገር ነው። እነዚህ ሰዎች ዘፍጥረት 1፡1 እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ መግቢያ እንደሚሰጥ

ይናገራሉ። ከዚያም ከ2-5 ያሉት ቁጥሮች እግዚአብሔር በፍጥረቱ የመጀመሪያ ቀን የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ የሚገልጹ ናቸው። እግዚአብሔር መፍጠር ከመጀመሩ በፊት፥ በፍጥረት መጀመሪያ ቀን ለሚቀጥሉት አምስት ቀናት ሥራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ አዘጋጀ ይላሉ። እግዚአብሔር ብርሃን ከመሥራቱ አስቀድሞ ቅርጽ የሌላት ባዶ ምድር ፈጠረ። ይህንን ምጣድ፥ የቡና ጀበና፥ ማድጋ፥ ወዘተ... ማበጀት ከመጀመሩ በፊት ለሥራው የሚያስፈልገውን ጭቃ ከሚያዘጋጀው ሸክላ ሠሪ ጋር ልናመሳስለው እንችላለን። ይህ አመለካከት ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር የበለጠ የሚስማማ ይመስላል።

በዘፍጥረት 1፡3-31 የሚገኘው የፍጥረት ታሪክ፥ እግዚአብሔር ቅርጽ ለሌላት ምድር እንዴት ቅርጽ እንደሰጣት የሚተርክ ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ባዶዋን ምድር በእንስሳትና በሰው ሞልቷታል። የፍጥረት ታሪክ እነዚህን ሁለት ነገሮች በቅደም ተከተል እንዴት እንዳሟላ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ተመልከት።

1 እግዚአብሔር ቅርጽ ላልነበራት ምድር ቅርጽ ሰጣት

2 እግዚአብሔር ባዶ የነበረችውን ምድር ሞላት።

1ኛ ቀን፡- ብርሃንና ጨለማ 4ኛ ቀን- የፀሐይ፥ የጨረቃ የከዋክብት፥ ወዘተ. ብርሃናት

2ኛ ቀን፡- ባሕርና ሰማይ 5ኛ ቀን- የባሕር እንስሳትና የሰማይ አእዋፍ

3ኛ ቀን፡- ደረቅ ምድር 6ኛ ቀን- የምድር ፍጥረታት አጥቢ እንስሳትና ሰው ከባሕር ተለየ፥ ዕፅዋት

የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል። አንደኛ፡- በመጀመሪያዎቹ ሦስት የፍጥረት ቀናት እግዚአብሔር ቅርፅ ለሌለው ነገር እንዴት ቅርፅ እንደሰጠ ልብ በል። ጨለማውን በመውሰድ ብርሃንና ጨለማ አድርጎ ለየ። እንዲሁም በመሀል የሰማዩን ግርዶሽ በማድረግ የምድርን ባሕር ከሰማይ በላይ ካለው ውኃ ለየ። በሦስተኛው ቀን ውኃን ከየብስ ለየና

በምድር ላይ ዕፅዋትን አበቀለ። ቅርፅ ያልነበራት ምድር አሁን መልክ አገኘችና በልዩ ልዩ ነገሮች ለመሞላት ዝግጁ ሆነች።

ሁለተኛ፥ በመጨረሳዎቹ ሦስት ቀናት እግዚአብሔር ባዶነቷን ሞላ። በመጀመሪያ፥ በአራተኛው ቀን እግዚአብሔር ፀሐይን፥ ጨረቃን፥ ከዋክብትን፥ ወዘተ. በሕዋው ውስጥ አስቀመጠ። ከዚያም በአምስተኛው ቀን በውኃ ውስጥ የሚኖሩትንና በሰማይ ላይ የሚበሩትን ፍጥረታት ፈጠረ። በስድስተኛው ቀን፥ እግዚአብሔር እንስሳትንና ሰውን በየብስ ላይ እንዲኖሩና ዕፅዋትን እንዲመገቡ አድርጎ ፈጠረ። እንዲሁም የመጀመሪያው ቀን ከአራተኛው፥ የሁለተኛው ቀን ከአምስተኛው፥ የሦስተኛው ቀን ከስድስተኛው ቀን ፍጥረት ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ መረዳት የሚያስደንቅ ነው። በአንደኛው ቀን እግዚአብሔር ብርሃን ሲሠራ፥ በአራተኛው ቀን እንደ ፀሐይ፥ ወዘተ. ለምድር ብርሃን የሚሰጡትን ነገሮች አደረገ። በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር ሰማይንና ባሕርን ሲሠራ፥ በአምስተኛው ቀን በእነዚህ ሥፍራዎች የሚኖሩትን ነገሮች ሠራ። በሦስተኛው ቀን የብስን፥ በስድስተኛው ቀን በየብስ የሚኖሩትን ነገሮች ሠራ።

11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዓለም በእግዚአብሔር የመፈጠሯን ሐቅ ክርስቲያኖች ማመን ያለባቸው ለምንድነው?

ለ) ክርስቲያን በእግዚአብሔር መፈጠሩን ሲያውቅ፥ ምላሹ ምን መሆን አለበት?

ሁለተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 1፡3-13

በዚህች ምድር በምንኖርበት ጊዜ፥ በሐዘንም ሆነ በደስታ ወቅት ልናስታውሰው የሚገባንና እጅግ አጽናኝ ከሆኑ እውነቶች አንዱ እግዚአብሔር በነገሮች ሁሉ ላይ ገዥ መሆኑ ነው። ረሃብን፥ ወይም የምድር መናወጥን የመሳሰሉ የተፈጥሮ ጉስቁልናዎች ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ አይደሉም። የቁስ አካላዊው አጥናፈ-ዓለም ፈጣሪ እንደመሆኑ፥ በነዚያ ላይ ሥልጣን አለው። ወይም ክፉ ሰዎች ሲያሳድዱን፥ እግዚአብሔር የሁኔታው ተቆጣጣሪ መሆኑን ልናስታውስ ይገባል። እንደዚሁም እግዚአብሔር የሰው ልጆች ሁሉ ፈጣሪ ነው። በፍጥረት ታሪክ ሁሉ ጸሐፊው ለእስራኤላውያን ለማሳወቅ የፈለገው

እውነትና እኛን ለማስተማር የፈለገው፥ እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ በመሆኑ፥ በምድር የሚሆነውን ሁሉ እንደሚቆጣጠር ነው። ታሪክንም ሁሉ የሚቆጣጠር አምላክ ነው።

12ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች በአስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ሲያልፉ፥ ይህ እውነት በምን መንገድ ሊያጽናናቸው ይችላል?

1. እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር በሚዘጋጅበት ጊዜ፥ ቅርጽ ለሌላት ዓለም ቅርጽ ሰጣት (ዘፍ. 1፡3-13)።

13ኛ ጥያቄ፡- ከዘፍ. 1፡3-13 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ፡-

ሀ) የእግዚአብሔር ቃል በፍጥረት ሥራ ውስጥ ምን ድርሻ ነበረው?

ለ) እግዚአብሔር ለዓለም ቅርጽ ለመስጠት በመጀመሪያ የተጠቀመው በምንድነው?

ሐ) እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን የሰየማቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?

መ) የመጀመሪያ ቀን ፍጥረትን በተመለከተ እግዚአብሔር ምን አለ?

ሠ) ለዓለም ቅርጽ ለመስጠት እግዚአብሔር ያደረገው ሁለተኛ ነገር ምን ነበር?

ረ) እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን የፈጠራቸው ሁለቱ ክፍሎች ምንድናቸው ብለህ ታስባለህ?

ሰ) እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን ለዓለም ቅርጽ ለመስጠት ምን አደረገ?

ሸ) ዕፅዋት እንዲበቅሉ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ቀ) እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ፍጥረታት የነበረው አመለካከት ምን ነበር?

በዘፍ. 1፡2 ላይ ጸሐፊው፥ ዓለም ቅርጽ የሌላት፥ ባዶና ጨለማ እንደ ነበረች ገልጿል። በዚህ ክፍል፥ እግዚአብሔር ጨለማን እንዴት እንደተቆጣጠረና ቅርጽ ለሌለው ቅርጽ እንደሰጠ እናያለን። እነዚህን

ቁጥሮች ስትመለከት፥ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች እንደሚያሳዩ ልብ በል። መጀመሪያ፥ ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዴት ዓለምን ሰው እንዲኖርባት አድርጎ እንዳዘጋጃት ያሳያል። ሁለተኛ፥ እውነተኛው አምላክ በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ያለውን ታላቅነት ያሳያል።

አንደኛ ቀን: -

የብርሃን ከጨለማ መለየት

ዓለም በጨለማ ተውጣ እግዚአብሔር እንዲሠራት ትጠብቅ ነበር። ጨለማ ለማንኛውም ሥራ ዕንቅፋት በመሆኑ ምክንያት እግዚአብሔር በፍጥረት ሥራው ውስጥ በመጀመሪያ ያደረገው በዓለም ላይ የጨለማን መጠን መገደብ ነበር። እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ጨለማን ፈጠረ አይልም። ጨለማ አስቀድሞ ነበረ። ብርሃንን ፈጠረና፥ ከዚያም ብርሃንና ጨለማን በሁለት ፈረቃ ለያቸው።

እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጥሮ እንዴት በቀላሉ ከጨለማ እንደለየው አስተውል። ብዙ ሰዓት አልወሰደበትም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በተናገረው ቃል ብርሃን ሆነ።

14ኛ ጥያቄ: - ሀ) ይህ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ምን ያስተምረናል?

ለ) ስለ እግዚአብሔር ቃል ኃይልስ ምን ያሳየናል? (ዕብ. 4:12፤ ኢሳ. 55:11 ተመልከት)።

እግዚአብሔር አንዳንዶች እንደሚያስተምሩት፥ የግል ባሕርይ የሌለው ኃይል ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር የሚናገር አምላክ ነው፤ እናም ቃሉ ኃይል የሌለው አይደለም። ይልቁንም ቃሉ ኃይሉን የሚገልጽ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በፍጥረት ወቅት ያልነበሩት ነገሮች ወዲያው እንዲሆኑና እንዲኖሩ አድርጓል። ዛሬም እንዲሁ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ያንኑ ተመሳሳይ ኃይል ይዞአል። እግዚአብሔር ኃያል እንደ መሆኑ መጠን፥ ቃሉም ኃይል አለው።

በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ተፈጠረ። ከዚያም እግዚአብሔር ብርሀንና ጨለማን ለያቸው። ብርሃኑን ‹ቀን› ብሎ ጠራው፤

ጨለማውንም ‹ሌሊት›። ለመጀመሪያ ጊዜ የቀንና የሌሊት ፈረቃ ተጀመረ። ብርሃኑ ምን ዓይነት እንደነበረ አናውቅም። ዛሬ በዓለማችን ብርሃን ከፀሐይ ይመጣል። ነገር ግን ፀሐይ እስከ አራተኛው ቀን ድረስ ስላልተፈጠረች፥ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ብርሃን ከፀሐይ፥ ከጨረቃና ከከዋክብት የመነጨ አይመስልም።

በዕብራውያን ባሕል፥ ለአንድ ነገር ስም ለማውጣት መቻል አውጪው በሚሰይመው ነገር ላይ ሥልጣን እንዳለው ያመለክታል። በኋላም አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም እንዳወጣ እናያለን። ይህም አዳም በእንስሳቱ ላይ ሥልጣን እንደነበረው ያመለክታል። በመጀመሪያ ግን ለነገሮች ስም ያወጣ የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ነበር። እርሱ ብቻ በብርሃናት ላይ ሥልጣን አለው።

ብርሃኑ ምን እንደነበረ ባናውቅም እንኳን፥ ምናልባት ከራእይ 22፡5 ምን ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ እናገኛለን። የመጨረሻውን ሰማይና ምድር አስመልክቶ ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «ለከተማዪቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራለት፥ መብራትዋ በጉ ስለሆነ፥ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም» (ራእይ 21፡23-24 ተመልከት) ይላል።

አንዳንድ ሊቃውንት ጨለማን የተለመደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክፉ ነገር ምሳሌ አድርገው ያዩታል (ዮሐ. 3፡19)። እግዚአብሔር ብርሃንን ሲፈጥር፥ በብርሃን ተገልጾ ክፉውን ሰይጣን የሚጥፋቱ ምሳሌ ነው ይላሉ።

‹ቀን› የሚለው ቃልም በሊቃውንት መካከል ክርክር አስነሥቷል። ቃሉ ዛሬ እኛ የምናውቀውን ሃያ አራት ሰዓታት ያመለክታል? ወይስ ብዙ ዘመናት ያዘለን ጊዜ? በዕብራውያን ዘንድ ቃሉ በአመዛኙ ሃያ አራት ሰዓታትን የሚወክል ቢሆንም፥ ከሁለቱ ለአንደኛው አማራጭ መግለጫ ሆኖ የሚያገለግልበት ጊዜም አለ። አንዳንድ ክርስቲያን ሳይንቲስቶች ይህን ክፍል ረጅም ጊዜ እንደወሰደ አድርገው ለማቅረብ ይፈልጋሉ፤ ይህም ከዘመናዊው የዓለቶች፥ የነዳጅ ዘይት ወዘተ. አፈጣጠር ትምህርት ጋር በይበልጥ እንዲስማማ በማሰብ ነው። ዳሩ ግን ከመጀመሪያው የፍጥረት ዕለት ጀምሮ ቀንና ሌሊት ስለነበረ፥ ዛሬ

እንደምናውቀው የሃያ አራት ሰዓታት ጊዜ ነው ብሎ መደምደሙ ከሁሉም የተሻለ ይመስላል። አለዚያ ቀናት ረጃጅም ጊዜያት ከሆኑ ሌሊቶችም እንደዚያው ይረዝማሉ ብሎ ማጠቃለሉ ተገቢ ይመስላል።

እግዚአብሔር ብርሃኑን ተመለከተና መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔር በፈጠረው ነገር ረክቶ ነበር።

ሁለተኛ ቀን :-

በምድር የደመናትና የውኃ መለየት

የመጀመሪያዋ ምድር በውኃ የተሞላች ነበረች። በዘፍ. 1:2 ጨለማ በጥልቁ ላይ ሲሆን፥ የእግዚአብሔር መንፈስም የውቂያኖሶችን መኖር በሚጠቁመው ውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር። ስለዚህ በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር በምድር ላይ ከነበረው ውኃ ወሰደና ምድርን ለሰው ተስማሚ መኖሪያ አደረገው። ውኃው በሁለት ዋና ዋና አካላት ተከፈለ። መጀመሪያ፥ ከውኃው የተወሰነ ክፍል ተከፍሎ ከአካባቢው አየር በላይ ተቀመጠ። ሁለተኛ፥ ቀሪው የውኃ ክፍል በምድር ላይ ተተወ። በሁለቱ የውኃ አካላት መካከል ሰማይ ነበር።

በሰማያት ያለው ውኃ ምን እንደሚያመለክት የተለያዩ አሳቦች አሉ። እንዳንዶች ውኃን በሰማይ እንደሚያዝሉ ደመናዎች አድርገው በማቅረብ፥ ከዚያም ዝናብ እንደምናገኝ ይገልጻሉ። ሌሎች ደግሞ ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ዓለም ልዩ እንደነበረች ያምናሉ። ከፀሐይ ከሚመጡ አደገኛ ጨረሮች ዓለምን ይከላከል የነበረ ከፍተኛ ውኃማ አካል በምድር ዙሪያ ነበረ ይላሉ። ከጥፋት ውኃ በኋላ በምድር ላይ የሰው ዕድሜ እየቀነሰ የመጣውም፥ ይህ የውኃ መሸፈኛ በጥፋት ውኃው ምክንያት በመወገዱ እንደሆነ ይናገራሉ።

እግዚአብሔር በሌሎች ቀናት እንዳለው፥ የዚህን ዕለት ፍጥረቱን መልካም ነው እንዳላለ አስተውል። ምናልባትም ይህ የሆነው እግዚአብሔር ምድርን ለመኖሪያነት በበቂ ሁኔታ ሠርቶ ስላልጨረሰ ይሆናል። ከሦስተኛው ቀን በፊት እግዚአብሔር የሠራውን ሁሉ «መልካም» ብሎ አልጠራም ነበር።

ሦስተኛ ቀን፡ -

የምድር መዘጋጀትና የዕፅዋት መፈጠር

በሦስተኛ ቀን፥ እግዚአብሔር ምድርን ለሰው መኖሪያነት ለማዘጋጀትና ቅርጽ ለመስጠት ሁለት ነገሮችን አደረገ። መጀመሪያ የብስን አዘጋጀ። ከዚህ በፊት መሬት በውኃ እንደተሸፈነች አይተናል። ስለዚህ እግዚአብሔር በምድር ላይ ላለው ውኃ ድንበር አበጀለት። ውቂያኖሶችን፥ ሐይቆችንና ወንዞችን መሠረታቸው። ዛሬ ከዓለም ሁለት ሦስተኛው እጅ ውኃማ አካል ነው። እንዲሁም በኋላ የሰው ልጅ መኖሪያ የሚሆነውን የብስ ሠርቷል።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ሁሉንም የዕፅዋት ዓይነቶች በምድር ላይ እንዲያድጉ ፈጥሯል። የእዚህ ክፍል ትኩረት ለምግብነት በሚውሉ አትክልቶች ላይ እንደሆነ መመልከቱ የሚያስገርም ነው። «ዘሩ ያለበትን ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ» የሚሉት ቃላት ባመዛኙ ለሰው ልጅ ለምግብነት ለሚውሉ ተክሎችና ዛፎች የተሰጡ ናቸው። በተጨማሪም በእዚህ ጊዜ ሌሎች ዕፅዋቶችም ተዘጋጅተው ነበረ። እግዚአብሔር ዕፅዋቶቹን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፥ ራሳቸው የሚራቡበትንም ብቃት በውስጣቸው አስቀምጦአል። እያንዳንዱ ተክል በፍሬዎቹ አማካይነት የሚራባበት ብቃት ተሰጥቶታል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር በዕፅዋት ላይ ያኖረውን ውስንነት ልብ በል። መራባት የሚችሉት «እንደ ወገናቸው» ብቻ ነበር። ይህ የአዝጋሚ ለውጥ ሂደትን በግልጽ የሚቃረን ነው፤ ምክንያቱም የነገሮችን የመለወጥ ብቃት ይወስናልና። ምንም እንኳ በአንድ በተወሰነ የዘር ዓይነት ላይ አንዳንድ ለውጦች ማድረግ ቢቻልም [በሳይንስ ኤስፒሽዩስ ይባላል] አንዱ ዘር ሌላ ዘር ሊያስገኝ አይችልም። ለምሳሌ ሊደረግ የሚችለው ለውጥ የስንዴን ዓይነት ጥንቃቄ በተመላበት ጥበብ ማሻሻል ነው። ይህ በእንስሳቱም ዓለም እንዴት እንደሚሠራ እንመለከታለን። ስለሆነም እግዚአብሔር ፍጥረትን መጀመር ብቻ ሳይሆን፥ በመራባት እራሳቸውን የሚተኩበትንም ብቃት በውስጣቸው አኑሮአል።

በዚህ ጊዜ ዓለም ቅርጽ ነበራት። እንስሳትና አዕዋፋት ይኖሩበት ዘንድም ዝግጁ ነበረች። በተለይም የሰው ልጅ መግዛት እንዲጀምር ሆና ተዘጋጅታ ነበር። ዕፅዋቶች በመፈጠራቸው የምድር ባዶነት ወደ ሙላት መለወጥ ስለ ጀመረ፥ ሦስተኛው ቀን የሽግግር ቀን ነው።

15ኛ ጥያቄ፡- ከመጀመሪያዎቹ የሦስት ቀናት ፍጥረቱ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?

ሦስተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 1፡14-25

2. እግዚአብሔር ባዶውን ዓለም ይሞላዋል (1፡14-31)

የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት ዓለምን ሕይወት ላላቸው ነገሮች መኖሪያነት በማዘጋጀቱ ላይ ሲያተኩሩ፥ የመጨረሻዎቹ ሦስት የፍጥረት ቀናት ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ እንዴት ዓለምን በተለያዩ ዓይነት ሕይወት ያላቸው ነገሮች እንደሞላት ይገልጻሉ።

16ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 1፡14-31 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ሰማያትን ለመሙላት ምን አደረገ?

ለ) በአራተኛው ቀን የተፈጠሩት ነገሮች ለምድር ምን አስተዋጽኦ አላቸው?

ሐ) እግዚአብሔር ሰማይንና ውኖችን ለመሙላት ምን አደረገ?

መ) እግዚአብሔር በአምስተኛው ቀን ለፈጠራቸው ነገሮች ምን ትዕዛዝ ሰጠ?

ሠ) እግዚአብሔር ምድርን ለመሙላት ምን አደረገ?

4ኛ ቀን - እግዚአብሔር ሰማያትን በተለያዩ ብርሃናት ሞላቸው።

በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር እንዴት ብርሃንን እንደፈጠረና ከጨለማ እንደለየው ተመልክተናል። በአራተኛው ቀን እግዚአብሔር ለመላው ዓለም ብርሃን የሚሰጡትን አካላት ፈጠረ። ታሪኩ የሚያተኩረው በሁለት ዓይነት ብርሃናት ላይ ነው። በመጀመሪያ፥ በቀን ጊዜ ብርሃን እንድትሰጥ ኃይል የተቸራት ትልቋ ብርሃን ፀሐይ ነበረች። በሁለተኛ ደረጃ፥ ሌሎች ትናንሽ ብርሃናት ነበሩ። እነዚህ በሌሊት የሚያበሩ ጨረቃና ከዋክብት ነበሩ።

የዘፍጥረት ጸሐፊ ሳይንቲስት ባለመሆኑ፥ ፍላጎቱ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ቀን የፈጠረውን ነገር በዝርዝር መግለጽ አልነበረም። ስለ ፍጥረት የተናገረው ሰው ከሚኖርበት ምድር ጋር ካለው ዝምድና አንጻር ብቻ ነው። እንዲሁም ፍጥረታቱን ለሰው ልጅ እንደሚታዩት አድርጎ ገለጻቸው እንጂ በትክክል ያሉበትን ሁኔታ አይደለም። አሁን የተለያዩ ብርሃን ሰጪ አካላት (ሶላር ሲስተሞች) እንዳሉ ከሳይንስ እንረዳለን። በእርግጥ ሳይንቲስቶቹም ቢሆኑ የአጽናፈ - ዓለሙን ዳርቻ አልደረሱበትም። ለእኛ ምንም ያህል ታላቅ ቢሆን፥ ሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው።

17ኛ ጥያቄ፡- ኢሳ. 40፡25-26 አንብብ። ሀ) እነዚህ ቁጥሮች በዚህ ዕለት ከተፈጠሩት ነገሮች ጋር ሲነጻጸሩ፥ የእግዚአብሔርን ታላቅነት እንዴት ያሳያሉ?

ለ) ይህ እግዚአብሔርን ወደማምለክ እንዴት ሊመራን ይገባል? እግዚአብሔርን ስለ ፍጥረቱ ታላቅነት ለማምለክ አሁን ጊዜ ውሰድ።

ለተፈጠሩት ብርሃናት ሦስት ዋና ዋና ተግባራት ነበሩዋቸው። መጀመሪያ፥ ቀንና ሌሊትን ለመለየት፤ ሁለተኛ፥ ምድርን በብርሃን ለማፍካት ሦስተኛ፥ ለወቅቶች፥ ለቀናትና ለዓመታት መፈራረቅ ምልክቶች ሆነው ለማገልገል። የፀሐይ፥ የምድር፥ እና የጨረቃ አቀማመጥ ምድርን በላቀ ሁኔታ ለማገልገል በሚችሉባቸው በትክክለኛ ሥፍራዎች ነው። በፀሐይ ዙሪያ ከሚገኙ ፕላኔቶች ሁሉ ውስጥ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች መያዝ የምትችል ምድር ብቻ ነች። ይህም የሆነው ከፀሐይ በትክክለኛ ርቀት ላይ የምትገኘው እርስዋ ብቻ በመሆኗ ነው። መሬት በፀሐይ ዙሪያ ስትዞር፥ የተለያዩ ወቅቶች እንዲፈራረቁ ታደርጋለች። ቀንና ሌሊት እንዲፈራረቅ የሚያደርገውም የመሬት በአራስዋ ዛቢያ ላይ መሽከርከር ነው። እንዲሁም የጨረቃ በምድር ዙሪያ መዞር በምድር ላይ ባሉት ወቅቶች ላይ ተፅዕኖ ያስከትላል። ይህን ሁሉ እንቅስቃሴ የቀመረው ጠቢቡ እግዚአብሔር ነው።

እነዚህ እንቅስቃሴዎች የማይዛነፉ በመሆናቸው፥ የሰው ልጅ ለዘመናት በፀሐይና በከዋክብት በመጠቀም ጊዜን ሲለካ ቆይቷል።

ተጓዦች አቅጣጫቸውን በፀሐይና በከዋክብት እገዛ ለመናገር ይችሉ ነበር። እነዚህ ነገሮች በትክክል የሚከናወኑ በመሆናቸው ወቅቶችን በተስተካከለ ሁኔታ ለማፈራረቅ ይችላሉ። በእውነቱ እነዚህ ሰው ከሠራው እጅግ ትክክለኛ ሰዓት በላይ ትክክለኞች ናቸው።

በአራተኛው ቀን መጨረሻ፥ ከምድር ከፍ ብሎ የሚታየው ሕዋ በሺዎች በሚቆጠሩ ከዋክብት፥ በተለያዩ ብርሃን ሰጪ አካላት (ሶላር ሲስተምስ)፥ ወዘተ. ተሞላ። ዛሬም እንኳ ሳይንቲስቶች በአጽናፈ - ዓለሙ ሁኔታ ይደነቃሉ። ምንም እንኳን በሚሊዮን ከሚቆጠሩ የብርሃን ዓመታት ወዲያ ዘልቀው ሌሎች የብርሃን አካላትን ለማየት ቢችሉም፥ እንዴት እንደተፈጠሩ ግን አያውቁም። አንዳንዶቹ ይህ ሁሉ በአጋጣሚ ተፈጠረ ለማለት ቢገደዱም፥ ለእኛ ግን ታላቁ ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዳዘጋጀውና እንደፈጠረው የማስተዋል ጥበብ ይነግረናል።

18ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 1፡18-21 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ ከፍጥረት የተነሣ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ነገር ምንድን ነው ይላል?

ለ) አጽናፈ - ዓለምን በተመለከተ፥ በሳይንስ ትምህርት የተማርሃቸውንና የእግዚአብሔርን ኃይል በማሳየት የበለጠ እንድናመልከው የሚረዱንን የተለያዩ እውነቶች ዘርዝር።

አምስተኛ ቀን :-

እግዚአብሔር ሰማይን በወፎች፥ ባሕሮችን ደግሞ በተለያዩ ፍጥረታት ሞላ።

በሁለተኛው የፍጥረት ቀን፥ እግዚአብሔር ከምድርና ከሰማያት በላይ ያሉትን ውኆች ለይቷል። በመካከሉም ጠፈር የተባለ ሥፍራ አበጅቷል። በአምስተኛው የፍጥረት ቀን፥ ሁለቱም ማለትም የሰማይ ጠፈርና ውኆች በተለያዩ ፍጥረታት ተሞሉ።

ለውኆች፥ እግዚአብሔር ጥቂት ዓይነት ፍጥረታትን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ዳሩ ግን ጸሐፊው እንደገለጸው እግዚአብሔር፥ «ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ» ብሏል። በመሆኑም እንደ ዓሣ፥

ዓሣ-ነባሪ፥ ወዘተ. የመሳሰሉ በዓይን የሚታዩ በርካታ ዓይነት ፍጥረታት ሁሉ በዚህ ቀን ተፈጥረዋል፤ እንዲሁም ደግሞ እንደ አሜባና ሌሎችም ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ጥቃቅን ፍጥረታትም ተፈጥረዋል።

ለሰማይ፥ እግዚአብሔር አምላክ የሚበርሩ ወፎችን ፈጥሮአል። ልክ ለዕፅዋቶች አምሳያቸውን የሚተኩበትን ኃይል እንደሰጠ ሁሉ፥ በውኃ ውስጥ ለሚገኙ እንስሳትና በሰማይ ላይ ለሚበርሩ አዕዋፋትም እንዲሁ እግዚአብሔር ይህንን ኃይል ሰጥቷቸዋል። ምንም እንኳ የሚራቡበት መንገድ ሊለያይ ቢችልም (ለምሳሌ፡- እንቁላል በመጣል፥ ወይም ልጅ በመውለድ)፥ እያንዳንዱ እንስሳ የመራባት ችሎታ አለው። ይሁን እንጂ የመራባቱ ሂደት የእራሱን ዝርያ ወይም አምሳያ በመተካት ብቻ የተወሰነ ነው። አሁንም፥ የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት አብይ አስተምህሮ በእነዚህ ጥቅሶች ተኮላሽቷል።

ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር ነገሮችን ስለ ባረከባት ሁኔታ እናነባለን። እግዚአብሔር በመጀመሪያ የባረካቸው ነገሮች ወፎችና በውኃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ነበሩ። በረከቱም በትዕዛዝ መልክ የተሰጣቸው ሲሆን ተራብተው አየሩንና ውኃውን መሙላት ነበረባቸው።

ስድስተኛ ቀን ፡- 1ኛ ክፍል -

እግዚአብሔር ምድርን በእንስሳት ሞላ (1፡24-25)

በሦስተኛው የፍጥረት ዕለት፥ እግዚአብሔር የብስና ዕፅዋትን ፈጥሯል። እንዲሁም ምድር በነዋሪዎች ለመሞላት ዝግጁ ነበረች። የ6ኛው ቀን ፍጥረት የመጀመሪያው ክፍል በምድር ላይ ስለሚኖሩ ፍጥረታት ይናገራል።

የቤት እንስሳት፥ በምድር ላይ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ሕይወት ያላቸውን ነገሮችና የዱር እንስሳት እግዚአብሔር እንዴት እንደፈጠራቸው ጸሐፊው ይገልጻል። ጸሐፊው በአንደኛ ደረጃ ያስቀመጣቸው ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑትን የቤት እንስሳት ነበር። እነዚህም ከብቶች፥ በጎች፥ ፍየሎች፥ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

የተፈጠረው ሁለተኛው ዓይነት ሕይወት «የመሬት ተንቀሳቃሽ» ነበር። ይህ የተሳቢዎችን - ማለትም የእባቦችን፥ ወዘተ. ፍጥረት የሚናገር ይመስላል። በመጨረሻም፥ ጸሐፊው ምድርን የሞሉዋትን የዱር አራዊት ይጠቅሳል።

ጸሐፊው የዓለምን ፍጥረታት የሚዘረዝርበትን ዓላማ ለመረዳት፥ ሰዎች በዚያን ዘመን ምን ዓይነት እምነቶች እንደነበሩዋቸው ማወቅ ያሻናል። ጸሐፊው ስለ ፍጥረት ጅማሬ መግለጽ ብቻ ሳይሆን፥ የእስራኤላውያንንም አስተሳሰብ ለመለወጥ እየሞከረ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ አሳብ እግዚአብሔር ብቻውን የዓለም ፈጣሪ እንደሆነ ነው። ፈጣሪ እንደ መሆኑ፥ ሕይወትን የሚሰጠው፥ ሕይወትን የሚያቆየውና ሕይወትን የሚያበቃውም እርሱ ነው [መዝ. (104) ተመልከት]። እርሱ ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን፥ ከፍጥረቱ፥ በተለይም ለእርሱ እጅግ በጣም አስፈላጊ ፍጥረት ከሆነው ሰው ጋር ከፍተኛ ህብረት ያደርጋል።

ዳሩ ግን እስራኤላውያን ብዙ አማልክት እንዳሉ ባስተማራቸው ባሕል ውስጥ አድገዋል። አብዛኛዎቹ እነዚህ አማልክት በተፈጠሩ ነገሮች ምሳሌ የተቀረጹ ናቸው። አማልክቱም እንደፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ ወይም እንደበሬዎች፥ ወይም ባሕር፥ ወዘተ. የመሳሰሉ ነበሩ። ስለሆነም፥ ሙሴ ለእስራኤላውያን እነዚህ አመለካከቶች እንዴት የተሳሳቱ እንደሆኑና እውነተኛና ፈጣሪ የሆነውን አምላክ ብቻ መከተል እንደሚያሻቸው ለማሳየት ይፈልጋል። የመጨረሻዎቹን ሦስት የፍጥረት ቀናት ብንመለከት፥ የጸሐፊውን አስተምህሮ ልንረዳ እንችላለን። በሙሴ ዘመንና በእኛም ዘመን እንኳ ሰዎች ለከዋክብት፥ ለፀሐይና ለጨረቃ ለመስገድ ይከጅላሉ። በሙሴ ዘመን፥ እነዚህ እንደ አምላክ ተቆጥረዋል። እርሱ ግን የእራሳቸው የሆነ ኃይል የሌላቸው ግዑዛን ፍጥረታት እንደሆኑ አስተምሯል። ብቸኛ ተግባራቸውም ቀናትንና ወቅቶችን ለማፈራረቅ እንደሰዓት ሆኖ ማገልገል ነው።

19ኛ ጥያቄ፡- ይህ ስለ ወደፊት ለመተንበይ በኮከብ ቆጠራ ስለሚመሩ ሰዎች ምን ያስተምረናል?

ሌሎች ደግሞ የዕፅዋትን አምላክ አምልከዋል። የተቀሩት ደግሞ እባቦችን፥ በሬዎችን፥ ዛፎችን፥ ወንዞችን፥ በአጠቃላይ የተፈጠሩ ነገሮችን አምልከዋል። እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር እንደተፈጠሩና አማልክት እንዳልሆኑ ሙሴ በግልጽ ያስተምራል።

እንዲሁም በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የተለያዩ ነገሮችን እንመለከታለን፡-

1. እግዚአብሔር የፍጥረት አካል ሳይሆን፥ ከፍጥረት ውጭ ስለሆነ፥ እርሱ ብቻ ዘላለማዊ ነው። እርሱ ጅማሬ የለውም። ሌሎች ነገሮች ሁሉ ግን ጅማሬ አላቸው።

2. በቃሉ ትዕዛዝ ብቻ ነገሮችን ወደ መሆን የሚያመጣው እግዚአብሔር ኃይልን የተሞላ አምላክ ነው። እንደእግዚአብሔር ሁሉ፥ ቃሉም ኃያል ነው።

3. እግዚአብሔር ሲሠራ፥ ሁልጊዜም ነገሮችን በጥሩ ሁኔታ ይሠራል። ከሁለተኛው ቀን በቀር፥ በእያንዳንዱ ቀን እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ሲመለከት፥ መልካም እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

4. እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ገዢ ነው። ምን እንደሚሆን ይወስናል፤ በዚያውም መሠረት ይፈጽመዋል።

20ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህ የእግዚአብሔር ባሕርያት በፍጥረት ታሪክ ውስጥ የታዩት እንዴት ነው?

ለ) ከላይ በተጠቀሱት ክፍሎች ውስጥ የታዩት ሌሎች የእግዚአብሔር ባሕርያት ምንድናቸው?

አራተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 1፡24-2፡3

ሳይንስን የበለጠ ባጠናን ቁጥር፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት በፈጠራቸው ነገሮች የበለጠ እንደነቃለን። ዛሬም እንኳን ሳይንቲስቶች ከእዚህ ቀደም ያልታዩትን አዳዲስ ነፍሳትንና እንስሳት እያገኙ ናቸው። ይሁንና እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ በአንድ ጊዜ የቃል ትዕዛዝ ብቻ ፈጠሯቸዋል። ምንኛ ታላቅ አምላክ ነው ያለን!

ትናንትና የመጀመሪያዎቹን 5 ቀን ተኩል ፍጥረት አጥንተናል። ዛሬ የ6ኛውን ዕለት የመጨረሻ ክፍል ፍጥረትና እንዲሁም እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ምን እንደሠራ እናጠናለን።

21ኛ ጥያቄ፡- ዘፍጥረት 1፡24-2፡3 አንብብ።

ሀ) ዘፍ. 1፡26ን ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?

ለ) የሰው ፍጥረት ብርቅዩ የሆነው እንዴት ነው?

ሐ) «የእግዚአብሔር አምሳል» ምን ይመስልሃል?

መ) እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ሥልጣን ምንድነው?

ሠ) ለመጀመሪያዎቹ ሰዎች እንዲበሉ የተሰጣቸው ነገር ምን ነበር?

ረ) እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የሰጣቸው ትዕዛዝ ምን ነበር?

ሰ) በሰባተኛው ቀን ምን ተደረገ?

በስድስተኛው ቀን፥ እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን ያዘጋጃትን ምድር በነዋሪዎች መሙላት ጀመረ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚኖሩትን እንስሳት ሁሉ ሠርቷል። ዳሩ ግን በስድስተኛው ቀን ደግሞ ከፍጥረታት ሁሉ እጅግ አስፈላጊ የሚሆነውን አንድ የመጨረሻ ፍጥረት ሠራ።

22ኛ ጥያቄ፡- መዝ. 8፡3-8 አንብብ። ሀ) ሰው ከምን ይበልጣል?

ለ) መዝሙረኛው ሰው በጥቂት እንዳነሰ የሚናገረው ከምንድነው?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር በፈጠራቸው የተለያዩ ፍጥረታት ሁሉ ብንደነቅም፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ፥ ከሁሉም በላይ የሚያስደንቀው የሰው ፍጥረት ነው። ይህም የታየው የዘፍጥረት ጸሐፊ የሰውን አፈጣጠር በተመለከተ ከሚሰጠው መግለጫ ውስጥ ነው። በጥናታችን የሚከተሉትን ነገሮች ለማየት እንችላለን፡-

1. የሰው ፍጥረት የሥላሴ አምላክ ሥራ ነው። በዘፍ. 1:26 እግዚአብሔር፥ «ሰውን እንፍጠር» እንዳለ እናነባለን። እንፍጠር የሚለው ቃል እነማንን እንደሚያመለክት ሊቃውንት ለረዥም ጊዜ ተከራክረውበታል። እግዚአብሔር ለመላእክት እየተናገረ ነው? ወይስ እግዚአብሔር ከእራሱ ጋር እየተማከረ ነው? ወይስ ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር አንድ ቢሆንም እንኳ፥ ሦስት የመሆኑን እውነት ፍንጭ እየሰጠ ነው? ሊቃውንት «እንፍጠር»ን በእነዚህ መንገዶች ተረድተውታል። ይሁን እንጂ፥ ከሁሉም የሚሻለው መረዳት ግን በብሉይ ኪዳን የተሰጠ ፍንጭ ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ለቀረበው ጠቃሚ እውነት መሆኑ ነው። ይህ አንዱ አምላክ እራሱን እንደ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የገለጸበት ነው። በዘፍጥረት ጥናታችን እየገፋን ስንሄድ፥ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ መረጃዎችን እንመለከታለን። እንዲሁም በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሰውን ለመፍጠር የተደረገውን ጥንቃቄ፥ እቅድ፥ አሳብ እንመለከታለን።

2. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ወይም ምሳሌ ተፈጥሯል። አሁንም ሊቃውንት በሰው ውስጥ የእግዚአብሔር አምሳል ምን እንደሆነ ተሟግተዋል። የምናውቀው አንድ ነገር ቢኖር ይህ በሥጋዊ አካል እንዳልሆነ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፥ እኛ ያለን ዓይነት ሥጋዊ አካል የለውም። ሥጋዊ ዓይኖች፥ ወይም እግሮች፥ ወይም እጆች የሉትም። ከሥጋዊ ሰው በፍጹም የተለየ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር «ያያል»፥ ወይም «ይይዛል» ሲል፥ ሥጋዊ ዓይኖቹን ወይም እጆቹን እየገለጸ አይደለም። ይልቁንም ጸሐፊው እግዚአብሔር የሚሠራውን ነገር ለእኛ ለማስረዳት ሊገባን በሚችለው ሰብዓዊ ቋንቋ እየተጠቀመ ነው። ይህ አምሳል ሊያካትታቸው የሚችላቸው ብዙ አማራጮች አሉ፡-

   ሀ) እግዚአብሔር ልክ እንደ ሰው እራሱን የቻለ አካላዊ ባሕርይ ያለው ነው። ይህም ማለት ከእንስሳት ወይ ዕፅዋት በተቃራኒ፥ ሰውና እግዚአብሔር ለማሰብ፥ ለማቀድ፥ ለማዘን፥ ወዘተ. ይችላሉ ማለት ነው።

ለ) ሰውና እግዚአብሔር፥ ሁለቱም ትክክልና ስሕተት የሆነውን ነገር የመምረጥ ብቃት አላቸው።

ሐ) ሰውና እግዚአብሔር፥ ሁለቱም ግንኙነት(ኮሚዩኒኬሽን) ለማድረግና አሳባቸውን ለመግለጽ ይችላሉ።

መ) እግዚአብሔርና የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች ቅዱሳንና ጻድቃን ነበሩ፤ ኃጢአትን አላወቁም ነበር።

ሠ) እግዚአብሔርና ሰው፥ ሁለቱም በሌሎች ላይ የመግዛት ብቃት ነበራቸው።

ረ) እግዚአብሔርና ሰው፥ ሁለቱም ቀድሞ ያልነበሩትን ነገሮች የመሥራት ችሎታ አበራቸው። ለምሳሌ ሰው መኪኖችንና አውሮፕላኖችን ሠርቷል። ይሁን እንጂ፥ ሰው ሁል ጊዜም እግዚአብሔር ከሰጠው ነገር ተጠቅሞ መሥራት አለበት።

ሰ) እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ ሁሉ፥ ሰውም ከመንፈስ ጋር ተፈጥሯል። ይህ ግዚአብሔርንና ሰውን ህብረት ለመፍጠር ያስችላቸዋል። ደግሞም መንፈሳዊው የሰው ክፍል ሊጠፋ ስለማይችል፥ ሰውን ዘላለማዊ ያደርገዋል።

እነዚህ ሁሉ በሰው ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን አምሳል ያንጸባርቃሉ ለማለት ንችላለን። ምንም እንኳ እንስሳት እጅግ በተወሰነ ደረጃ ከእነዚህ አንዳንዶቹን ለማድረግ ቢችሉም (ለምሳሌ መግባባት)፥ ሰው ያለውን ያህል ብቃት የላቸውም።

ይህ አምሳል በአዳምና ሔዋን ውድቀት ምክንያት በሰው ሕይወት ውስጥ ተበላሽ። ይሁን እንጂ፥ አሰው ልጅ አሁንም በእግዚአብሔር አምሳል ይኖራል። ለደኅንነት ከእግዚአብሔር እቅዶች አንዱ አካል እኛን ዳግም በአምሳሉ በማበጀት የተበላሸውን ሕይወት ማደስ ነው (ቆላ. 1፡15፤ ዕብ. 1፡3፤ ሮሜ 8፡29፤ 2 ቆሮ. 3፡18 ተመልከት)።

3. እግዚአብሔር ለሰው በምድር ላይ በሚገኙ በፍጥረታት ሁሉ ላይ የመግዛት መብት ሰጥቶታል። በዓሶች፥ በወፎች፥ በቤት እንስሳትና በምድር ላይ በሚኖሩ በሌሎች ሁሉ ላይ ሥልጣን አለው።

4. ሁለቱም ሴትና ወንድ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸውን መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ይህም ሴትንና ወንድን በብቃት፥ በጠቀሜታ፥ ወዘተ. በእግዚአብሔር ፊት እኩል ያደርጋቸዋል።

23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንዶች ሴቶችን ከወንዶች ከሚያነጻጽሩበት ሁኔታ ይህ አስተሳሰብ የሚለየው እንዴት ነው?

ለ) የእግዚአብሔር አምሳል ምን እንደሆነ ያለን መረዳት፥ ሴቶችን፥ የሌላ ነገድ ሰዎችን፥ ያልተማሩትን ሰዎች፥ ወዘተ. እንዴት እንድንመለከት ያደርገናል?

በሁሉም ባሕል ውስጥ ፍትሕ-አልበኝነትና በዘር መመጻደቅ አለ። ለክርስቲያኖች እነዚህ ኃጢአቶች ስለሆኑ፥ ልናስወግዳቸው ይገባል። እግዚአብሔር ሰውን በእራሱ አምሳል ከሠራበት ሁኔታ ውስጥ ልንማራቸው የሚገቡ አስፈላጊ እውነቶች አሉ። አንደኛ፥ ሴቶች የወንዶች የበታች ናቸው ብሎ ለማመን የሚያስደፍር ምንም ምክንያት የለም። ሁለቱም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል እንጂ ወንድ ከሴት የበለጠ የእግዚአብሔር አምሳል አልተቀበለም። ወንዶችና ሴቶች እኩል የመሆናቸው መረዳት እግዚአብሔር ሁለቱንም በአምሳሉ ከፈጠረበት ሁኔታ ድጋፍ ያገኛል።

ሁለተኛ፥ ዘረኝነት ምንም ሥፍራ የለውም። ጥቁር፥ ቀይ፥ ወይም ነጭ ብንሆን፥ ሁላችንም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረናል። በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል ለዘር መድልዎ ወይም መመጻደቅ ሥፍራ የለውም (ገላ. 3:28)።

ሦስተኛ፥ በማኅበረሰቡ ውስጥ ባለን ደረጃ መኩራራት ሥፍራ የለውም። ሀብታም ወይም ድሀ፥ የተማረ ወይም መሐይም፥ ጤነኛ ወይም አካለ-ስንኩል፥ ሁሉም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል።

24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች እነዚህን ሦስት እውነቶች በማስተዋል የማይመላለሱት ለምንድነው?

ለ) በሕይወታችን፥ ወይም በቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሦስት እውነቶች በተግባር ለመተርጎም ምን ለማድረግ እንችላለን?

ሐ) ሰዎች አጉል የሆኑ ባሕላዊ አመለካከቶችን እንዲያስወግዱ ለመርዳት በቤተ ክርስቲያን ምን ለማስተማር እንችላለን?

እንደ ዕፅዋቱና እንስሳቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ሰዎችን ከመባረኩም በላይ የመጀመሪያም ትዕዛዝ ሰጥቷቸዋል። ሁለት ነገሮችን እንዲያደርጉ አዝዞአቸዋል። መጀመሪያ፥ በቁጥር እንዲበዙ አዘዛቸው። እንደእንስሳቱ ሁሉ፥ ሰውም በእራሱ የመራባት ብቃት አለው። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በምድር የእርሱ ተወካይ ሆኖ እንዲገዛ አዘዘው። እግዚአብሔር ሰው ምድርን እንዲያበላሽ መብት ስላልሰጠው፥ አገዛዙ ምን ዓይነት አገዛዝ መሆን እንደነበረበት በሚቀጥለው ሳምንት እንመለከታለን።

እንዲሁም እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚገኙትን ዕጽዋት ሁሉ ለሰው ልጅ ለምግብነት ሰጠው። የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት ሥጋ መብላት አያስፈልጋቸውም ነበር። ይልቁንም ዕጸበል ነበሩ። እንደ ሌሎቹ እንስሳት ሁሉ አትክልቶችን መመገብ ነበረባቸው።

የእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራ በሰው መፈጠር ከፍጻሜ ደረሰ። የሰውን ፍጥረት በተመለከተ እግዚአብሔር መልካም ብቻ ሳይሆን፥ «እጅግ መልካም» እንደ ነበር ተናግሯል። እግዚአብሔር በተመለከተው ነገር ተደስቶና ረክቶ ነበር።

በሚቀጥለው ሳምንት እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን በፈጠረበት በስድስተኛው ቀን ምን እንዳደረገ ይበልጥ ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን። እርግጥ የዘፍጥረት1. ዓላማ፥ የዓለምን አፈጣጠር ጠቅለል ባለ መልክ መግለጽ ነው። ጸሐፊው ስለ ፍጥረት ብዙ መጻሕፍት ለመጻፍ ይችል ነበር። ዳሩ ግን ጸሐፊው የሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ እየጻፈ አልነበረም። ፍላጎቱ እስራኤላውያንና እኛም ሁላችን ፍጥረት ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደመጣ እንድንገነዘብ ነው። መልካምና የሚያስደስት ምንባብ ቢሆንም፥ ከሁሉም በላይ ግን፥ ፈጣሪ አምላክን ለማመስገንና ለማክበር የሚገፋፋን ነው።

25ኛ ጥያቄ፡- የፍጠረትን ታሪክ የበለጠ መረዳት፥ የእግዚአብሔርን ኃይል በበለጠ ወደ መረዳትና እግዚአብሔርን በበለጠ ወደ ማመስገን የሚመራን እንዴት ነው? ዓለምን የመግዛት

ትክክለኛ አመለካከት ሰዎች ምድርን አለ አግባብ ከመጠቀምና ከማጥፋት ይልቅ እንክብካቤ እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸው በምን መንገድ ነው?

26ኛ ጥያቄ፡- የአጽናፈ-ዓለሙ ምንጭ እግዚአብሔር መሆን፥ ወይም የሕይወት-አልባው ቁስ-አካል (የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት) ውጤት መሆን፥ ምን ለውጥ ያመጣል?

ሰባተኛ ቀን፡ -

የሰባተኛው የዕረፍት ቀን መቋቋም (2፡1-3)።

የእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራ በሰው መፈጠር ከፍጻሜ ደርሷል። ዛሬ የምንደሰትባቸውን ነገሮች ሁሉ በሰማያትና በምድር ላይ ፈጥሯል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ‹ዐረፈ› ይላል።

‹ዕረፍት› የሚለው ቃል እግዚአብሔር በሥራው ብዛት ደክሞ እንዳረፈ የሚገልጽ አይደለም። የፍጥረት ሥራ የእግዚአብሔርን ጉልበት አላዳከመም ነበር። ሁሉም የተፈጠረው በቃሉ ኃይል እንደ ነበር አስታውስ። ይልቁንም በዚህ ጊዜ የተጠቀሰው የ‹ዕረፍት› አሳብ የፍጻሜና በዓል የማድረግ አሳብ ያዘለ ነው። በዚህ ጊዜ የፍጥረት ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተፈጽሞ ነበር። እግዚአብሔርም በተሠራው ሥራ ደስ ተሰኝቶ ነበር። ዓለምን፥ ውበቷን፥ ሰላሟን፥ እና በውስጧ ያለውን ሁሉ በመመልከት ደስ ተሰኘ። በተለይም በአምሳሉ ከተፈጠረው የሰው ልጅ ጋር ሕብረት ማድረግ ያስደሰተው ነበር።

እንዲሁም እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከ፤ ለእርሱ የተለየ ቀን ሆነ። ‹ቀደሰው›ም። በእዚህ ሥፍራ ‹ቀደሰው› የሚለው ቃል ለተለየ ዓላማ መለየቱን ያመለክታል። ሰው በእግዚአብሔር ፍጥረታት ለመደሰትና፥ ከሁሉም በላይ ፈጣሪውን ለማምለክ ከሥራው የሚያርፍበት ቀን ሆኖ ተለየ።

‹ሰንበት› ተብሎ የተጠራው ሰባተኛው ቀን ቅዳሜ፥ በኋላ አይሁዶች እንዲከተሉት እግዚአብሔር ያዘዘው ትልም ሆነ (ዘጸ. 20፡8-11)።

እነርሱም እንደ እርሱ በዚህ ዕለት ሥራቸውን አቁመው በበዓሉና በአምልኮ ላይ ማተኮር ነበረባቸው።

27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰንበት የሚለው ቃል በአማርኛ ምን ማለት ነው?

ለ) አንዳንድ ሰዎች እሑድን ሰንበት ብለው የሚጠሩት ለምድነው? ይህስ ትክክል ነው?

ሐ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ቅዳሜ የአምልኮ ዕለት መሆን እንዳለበት የሚናገሩት ለምንድነው?

አንዳንድ ክርስቲያኖች ቅዳሜ ሳይሆን በእሑድ ቀን ለምን እንደምናመልክ ትልቅ ጥያቄ አላቸው። ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች በቅዳሜ ቀን ማምለክና በተጨማሪም አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን መጠበቅ እንዳለብን ይናገራሉ። መልሱ የሚገኘው ከአዲስ ኪዳን ነው። ክርስቲያኖች ልክ እንደ አይሁዶች በዕለተ-ቅዳሜ ለማምለክ የማይገደዱባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ።

1. በሁሉም ቀናት ለማምለክ ስለምንችል፥ ለክርስቲያን፥ ቀናት ሁሉ ቅዱስ ናቸው። በቆላ. 2፡16-17 ጳውሎስ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ፥ ወይም ስለ በዓል፥ ወይም ሰለወር መባቻ፥ ወይም ስለ ሰንበት፥ ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው» በማለት ጽፎአል (ሮሜ 14፡5-8 ተመልከት)። ከሁሉም የሚበልጠው የምናመልክበት ቀን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናችን፥ እግዚአብሔርን ለማምለክ ጊዜ መመደባችን ነው።

2. ክርስቲያኖች የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ለማክበር በየእሁዱ ይሰበሰባሉ። ኢየሱስ ከሙታን የተነሣው በእሑድ ቀን ስለሆነና ያም እግዚአብሔር የኢየሱስን ፍጹም መሥዋዕት የተቀበለበት ዕለት ስለሆነ፥ ያንን ቀን እናከብራለን። ከጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጀምሮ፥ ‹የጌታ ቀን› ብለው በመጥራት፥ ክርስቲያኖች አምልኮአቸውን በዕለተ-እሑድ ያካሂዱ ነበር (የሐዋ. 20፡7፤ ራእይ 1፡10 ተመልከት)።

28ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፡- ዮሐ. 1፡1-5፤ ቆላ. 1፡13-20፤ ኢዮብ 33፡4፤ መዝ. (104)፡30።
ዓለምን እንደፈጠረ የተነገረለት ማነው?

ዓለምን የፈጠረው ማነው? ግልጹ መልስ እግዚአብሔር ነው የሚል ነው። ከሥላሴስ ውስጥ፥ ዓለምን የመፍጠር ሚና የተጫወተው ማነው? መጽሐፍ ቅዱስ ሦስቱም የሥላሴ አባላት በፍጥረት ሥራው ውስጥ በንቃት እንደተሳተፉ ያስተምራል። እግዚአብሔር አብ እንደ ፈጣሪ መታየቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው። ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ ድርሻ እንደ ነበረው እንመለከታለን። በተጨማሪም አዲስ ኪዳን ሁሉም ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጠረ ይናገራል።

29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በዘፍ. 1 ጥናታችን ውስጥ የምናገኛቸው ዋና ዋናዎች ትምህርቶች ምንድናቸው?

ለ) እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ከሆነ፥ ከእርሱ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረን ይገባል?

ከዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ የምናገኘው አቢይ ትምህርት ምንድነው? ሁል ጊዜም አምላካችን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማስታወስ አለብን። በሰው አምሳል የተፈጠረ ደካማ አምላክ አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔር ኃይልን ሁሉ የተሞላና የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ አምላክ ነው። እርሱ ጅማሬ የለውም። ሁሉም ነገሮች ለእርሱ ክብርና ምስጋና ለማቅረብ ተፈጥረዋል። እኛም የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ነን። እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ሲሆን፥ እኛ ደግሞ ፍጥረቶቹ ነን። ሰዎች የቱን ያህል ቢሰለጥኑ፥ ምንም ያህል ታላቅ ነገር ቢያደርጉ፥ ምን ጊዜም የፍጥረት አካል መሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው። የእግዚአብሔር ፍጥረት እንደመሆናችን፥ ፈጣሪን ማክበርና መታዘዝ አለብን። በየዕለቱ ፈቃዳችንን አባታችን ለሆነው ለእርሱ በማስገዛት፥ በነገር ሁሉ እርሱን ለመታዘዝ መሻት አለብን። ግን ይህንን እያደረግን ነውን? አንድ ሰው እንደ ተናገረው እግዚአብሔር በሁለት መንገዶች የእኛ ባለቤት ነው። በፈጣሪነት መብቱና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እኛን በመግዛቱ ሁለት ጊዜ የራሱ ንብረት አድርጎናል። «በዋጋ

ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፡ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1 ቆሮ. 6፡19-20)።

30ኛ ጥያቄ፡- ሁል ጊዜም እግዚአብሔርን ፈጣሪህና አዳኝህ አድርገህ በመገዛት ብትመላለስ፡ ሕይወትህ እንዴት አድርጎ መለወጥ እንደሚችል ግለጽ።

አምስተኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከመከለስ በተጨማሪ ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. የጸሎት ጊዜ

3. ትምህርቱን መከለስ

4. የውይይት ጊዜ።

ሀ. 1) በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት አስፈላጊ የሆኑ አራቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች እንዴት በዛሬው ትምህርት ውስጥ እንደተንጸባረቁ ግለጽ።

2) አራቱንም አበይት የጥናት ጥያቄዎችን በሙሉ ሊያንጸባርቁ ስለሚችሉ ሌሎች ጥያቄዎች መግለጫዎች ስጥ።

ለ. 1) የዓለምን ጅማሬ በተመለከተ የአዝጋሚ ለውጥ ሂደትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አነጻጽር።

2) ዓለም በእግዚአብሔር እንደተፈጠረች እንጂ በአዝጋሚ የለውጥ ሂደት እንዳልተገኘች ለምን ክርስቲያኖች እንደሚያምኑ ሊሰጡ የሚችሉዋቸው አንዳንድ መልሶች ምንድናቸው?

ሐ. ከዘፍ. 1-2፡3 ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?

መ. መዝ. (19)፡ 1-4 እና ሮሜ. 1፡18-23 አንብብ።

1) የፍጥረት ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረናል?

2) የፍጥረትን ታሪክ ማወቅ ሰውን ወደ ደኅንነት ለመምራት በቂ ይመስልሃል? ግለጽ።

ሠ. 1) በዘፍ. 1 ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች ምንድናቸው?

2) ይህ ክፍል ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ያስተምራል?

3) ይህስ በዛሬው ሕይወታችን ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

ረ. 1) በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር አምሳል ምንድነው?

2) ይህ በሕይወታችን ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

3) እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በፈጠራቸው ጊዜ ከነበረው አምሳል፥ የአሁኑ የሰው ሁኔታ የሚለየው እንዴት ነው?

4) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የአጉል ጥላቻ አመለካከቶች ምሳሌዎች ዘርዝር።

5) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የአድልዎ ምሳሌዎች ዘርዝር።

6) በውስጥዋና በኢትዮጵያ የሚገኘውን አድልዎ ለማስወገድ ቤተ ክርስቲያንህ ምን እያደረገች ነው?

ሰ. እግዚአብሔርን ስለ ፍጥረቱ የምታመልክበት የተወሰነ ጊዜ መድብ።

5. ጸሎት።

ትምህርት ሦስት

ዘፍ. 2፡4-4፡26

የመጀመሪያ ቀን፡- ዘፍ. 2፡4-25

ባለፈው ሳምንት ዘፍ. 1-2፡3 አጥንተናል። እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ የተሰጠውን ጠቅለል ያለ ትምህርት ያቀርባሉ። ዛሬ በዓለም ውስጥ የሚታየውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንዴት በ6 ቀናት ውስት እንደ ፈጠረ ያስተምራሉ።